## ገንዘብን የት ልንቆጥብ እንችላለን?

ገንዘባችንን የምንቆጥብበት ቦታ በቀጣይ ልናገኝ የምንችለዉን የወለድ መጠንና የደህንነት አስተማማኝነቱን ይወስነዋል፡፡

- መኖሪያ ቤታችን ባለ ድብቅ ቦታ በማስቀመጥ ልንቆጥብ እንችላለን፤ ይህን ማድረግ ግን ደህንነቱ አስተማማኝ አይደለም፤ወለድም አናገኝበትም
- በአግባቡ የተደራጁ የገጠር የቁጠባና ብድር ተቋማት ለምሳሌ እንደ ዕቁብ በመግባት መቆጠብ ይቻላል፤ ደህንነቱም አስተማማኝ ነው
- ቋሚ ንብረቶችን ለምሳሌ በሬ ወይም ላም በመግዛት መቆጠብ ይቻላል፤ ምንአልባት ግን የገዛነው ቋሚ ንብረት ዋጋዉ ሊቀንስ ወይም ሊሞት ይችላል
- በገንዘብ ተቋማት ማለትም እንደ ባንክ ወይም የብድርና ቁጠባ ማህበራት መቆጠብ ይቻላል፤ ይህ የቁጠባ ዘዴ ደህንነቱ አስተማማኝ ነው፡፡ እንዲሁም ተጨማሪ ወለድም ያስገኛል፡፡

## ገንዘብን በአግባቡ ማስተዳደር



- በየዕለቱ የምንወስናቸው ውሳኔዎች አሁን ያለንና የምንቆጥበው ገንዘብ መጠን ላይ ተጽኖ ያደርጋሉ
- ገቢና ወጪያችንን በደብተር በመመዝገብ ስለገንዘብ አስተዳደር የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል
- የምንቆጥበውን ገንዘብ ለምን እንደምናውለው ማቀድ ይገባናል

## ገንዘብ የመቆጠብ ጥቅም



- ከብድር ጋር የተያያዙ ወጪዎችን ይቀንሳል
- ወደፊት ለሚመጣው ጊዜ ዋስትና ይሆናል
- ገንዘብ አስተማማኝ ቦታ እንዲቀመጥ ያደርጋል
- የመዋዕለ ንዋይ ፍሰትን በአግባቡ ለማካሄድ ይረዳል
- የአልታሰቡ ወጭዎችን ለመሸፈንና ለክፉ ቀን ደራሽ ይሆናል
- ብድር የማግኘት እድልን ይጨምራል
- እንደ በሬና ላም እንዲሁም ሌሎች ቋሚ ንብረቶችን ለመግዛት ያስችላል
- የወለድ ገቢ ያስገኛል

## ለበለጠ መረጃ

የገንዘብ ቁጠባን በተመለከተ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ በአካባቢዎ የሚገኙ የብድርና ቁጠባ ተቋማትን ወይም ባንኮችን ያነጋግሩ፡፡

# የቁጠባ ጥቅም



- ስለ ገንዘብ አስተዳደር ማውራት ለምን ያስፈልጋል?
- ገንዘብ መቆጠብ ለምን ያስፈልጋል?
- እንዴትና የት ነው ገንዘብን ልንቆጥብ የምትችለዉ?

እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ የቁጠባን ጥቅምና አስፈላጊነት ያሳየናል፡፡

"ከሰሊጥ የማገኘዉ ገቢ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ አመት ከማገኘው ገቢ ከፍተኛ ወጪ ለሚጠይቀኝ ለሚቀጥለዉ ዓመት የእርሻ ስራዩ መቆጠብ ይኖርብኛል፡፡ ይህንን ካላደረኩ በሚቀጥለው የምርት ዘመን ከፍተኛ ወለድ ከሚያስከፍሉ አራጣ አበዳሪዎች መበደር ግድ ይለኛል፡፡ ስለሆነም ሰሊጤን ስሸጥ ከማገኘው ገቢ ለሚቀጥለው አመት ለእርሻ አገልግሎት የሚያስፈልገኝን ብር ከወዲሁ መቆጠብ አለብኝ፡፡"

ሰሊጥ አምራች አርሶ አደር ቅባቱ

## ስለ ገንዘብ አስተዳደር ማውራት ለምን ያስፈልጋል?



ሁላችንም ከተለያዩ ገቢዎች ገንዘብ እናገኛለን እንዲሁም ለተለያዩ ወጪዎች ገንዘብ ወጪ እናደርጋለን፣ ነገር ግን ብዙዎቻችን ገንዘባችንን በአግባቡ አናስተዳድርም፣

- ሁላችንም የተለያዩ ወጪዎችን ለመሸፈን ገንዘብ ያስፈልገናል፡- ለምግብ፣ ለልብስ፣ ለሳሙና እንዲሁም በዕለት ተዕለት የሚያስፈልጉን ነገሮችን ለማሟላት ገንዘብ እናወጣለን
- ያሰራናቸዉን የቀን ሰራተኞች ለመክፈል፣ ማዳበሪያ ለመግዛትና ለመሳሰሉት ወጪዎች ገንዘብ ልንበደር እንችላለን
- ገንዘብ ከሰሊጥ ሽያጭ እናገኛለን
- ለልጆቻችን ትምህርት ማስተማሪያ፣ ለህክምና ወጪ እና ሌሎች ጉዳዮችን ለማሟላት ገንዘብ መቆጠብ ያስፈልገናል፡፡

## ገንዘብን መቆጠብ ለምን ያስፈልጋል?



- ቁጠባ እንደ ምግብና ልብስ የመሳሰሉ የየዕለት መሰረታዊ የቤት ዉስጥ ፍጆታዎቻችንን እንድናሟላ ያስችለናል
- ቁጠባ ውድ የሆኑ ንብረቶችን ማለትም በሬዎችን፣ ላሞችን፣ ምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ ለመግዛት ያገለግለናል
- ቁጠባ ቀድመው ያልታሰቡ እና ያልታዩ ድንገተኛ ወጪዎችን ለምሳሌ ለድንገተኛ ህመም ህክምናና ሃዘን የመሳሰሉ ወጪዎችን ለመሸፈን ይረዳል
- ቁጠባ ወደፊት ለምናወጣቸው ወጪዎች ለምሳሌ የልጆቻችን ትምህርት ቤት ወጪን ለመሸፈን ያስችለናል
- ተቋማት ብድር ከማበደራቸዉ በፊት የተበዳሪውን የመቆጠብ አቅምና ልምድ ያያሉ፡ ስለዚህ ቁጠባ በቀላሉ ብድር መበደር እንድንችል ያስችለናል
- ቁጠባ ገንዘብን አስተማማኝና ስጋት የሌለበት ቦታ እንድናስቀምጥ ይረዳል

## እንዴት ገንዘብን መቆጠብ እንችላለን?

መቆጠብ ከመጀመራችን በፊት ምን ያህል ገቢ እንደምናገኝና ምን ያህል ገንዘብ ወጪ እንደምናደርግ ማወቅ አለብን፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ጥያቄዎች እራሳችንን እንጠይቅ፡-

- ምን ያህል ገንዘብ ወይም ገቢ አገኛለሁ?
- ከማገኘው ገቢ ውስጥ ምን ያህል ገንዘብ ለዕለት ወጪ ያስፈልገኛል?
- በቀጣይ ምን አይነት ወጪ ላወጣ ወይም ምን ልገዛ እችላለሁ?
- ለወደፊቱ የሚያስፈልገኝን ገንዘብ ለማግኘት ምን ያህል መቆጠብ እችላለሁ?

የየዕለት የጥሬ ገንዘብ ገቢና ወጪያችንን መመዝገብ ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች ለማወቅ ያግዘናል፡፡

